# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 151 መጋቢት 29 2003 ገጽ 1


**ጊዜው ደርሷል!!!! የሁላችን የጋራ ጠላት በሆነው በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ የምንነሳበትና ነፃነታችንን የምንቀዳጅበት ቀን ደርሷል!!! በዚያ ቀን በጋራ መቆም አለብን። ትግላችን ቀናትን ሳይሆን ሳምንታትን ምናልባትም ወራትን ይፈጅብን ይሆናል። ድል ሳናደርግ ወደ ቤት መመለስ ግን የለም።**

**በየቋንቋዎቻችን "በቃ!!!" እንበል!!!!**

**በቃ!!! ገዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጉደስ!!!**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በአገሪቱ ውስጥ እየተስፋፋ በመጣው ህዝባዊ መነቃቃት የተደናገጠው ዘረኛው መለስ ዜናዊ ተቃዋሚዎች ላይ ዛተ

ማክሰኞ መጋቢት 27 ቀን 2003 ዓም ተደርጎ በነበረው የወያኔ ሸንጎ ላይ ለህዝብ ተወካይ ተብዬው የተለመደውን ዲስኩር ያሰማው መለስ ዜናዊ በአገሪቱ ውስጥ እየተስፋፋ የመጣው ህዝባዊ ብሶት ፈንድቶ የስልጣን ዕድሜውን እንደሚያሳጥር በመስጋት ከተጠራቀመው የህዝብ ብሶት ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸውን የኤርትራ መንግሥት እና በአገር ውስጥ በሠላም እንታገላለን የሚሉትን ተቃዋሚ ሃይሎች በጅምላ ሲወነጅል ተስተውሎአል።

መለስ ዜናዊ በከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጥ መሆኑን መደበቅ ባልቻለበት በዚህ የሸንጎ ንግግሩ፤ እስትንፋሹ እየተቆራረጠ "በአገራችን ውስጥ እየተካሄደ ያለው ልማት እንዲጨናገፍና ሰላም እንዲናጋ ግብጽ በኤርትራ መንግሥት አማካይነት ነጭ ለባሾችን አገሪቱ ውስጥ በማሰማራት አመጽ እና ሽብር ለመጫር ተግታ እየሰራች ነው" በማለት ህዝባችን ለሃያ አመት ያከማቸው ብሶት ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸውን የውጪ ሃይሎች ሲከስ ታይቶአል። የአዕምሮ አለመረጋጋት በሚፈጥረው የስነልቦና ጭንቅት እርስ በርሱ በሚጋጭ ቃላት አንዴ "አዲስ አበባን ባግዳድ የማድረግ አላማ አላቸው" ወዲያው እጥፍ ብሎ ደግሞ "ኢሃደግን ከሥልጣን የማባረር (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ የግፍ አገዛዝ ያበቃ ዘንድ ህዝብ ለነጻነቱ እንዲነሳ የሚቀሰቅሱ ተባራሪ ወረቀቶች መበተን ቀጥሎአል

የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ዘገባ ለሃያ አመታት ተንሰራፍቶ የኖረው የወያኔ የግፍ አገዛዝ ያበቃ ዘንድ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ጥሪ የሚያደርግ በራሪ ወረቀት መሰራጨት ጀምሮአል።

በአዲስ አበባ፤ በአዋሳ፤ በኮምቦልቻ፤ በአርባምንጭ፤ በደሴ፤ በድሬደዋ እና ሌሎች ከተሞች የተበተኑት እንዚህ በራሪ ወረቀቶች ህዝብ ለአገሩ አንድነትና ለነጻነቱ ሲል ወያኔ እያደረሰ ያለውን የጥፋት ተልዕኮ ለማስቆም ሆ ብሎ መነሳት ያለበት ጊዜው አሁን መሆኑን የሚያመለክት ነው ተብሎአል። ህዝብ በብዛት ይሰበሰብበታል ተብሎ በሚታሰብባቸው ቦታዎች በመበተን ላይ ያለውን ይህንን በራሪ ወረቀት ማን እንደሚበትነው ወያኔ ቀርቶ ዜጎችም ሊያውቁ እንዳልቻሉ በዚህም የተነሳ በህቡዕ የተደራጀ አንድ ሃይል ከበስተጀርባው ልኖር እንደሚችል ወረቀቶቹ በተበተነባቸው ከተሞች ያሉ ነዋሪዎች ይናገራሉ።

ከሁለት ሳምንት በፊት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የ6 ኪሎ ግቢ መበተን የጀመረው ይህ በራሪ ወረቀት በሌሎች የአዲስ አበባ ክልሎችም እንደተስፋፋና ከትናንትና ወዲያ ማክሰኞ ጠዋት ደግሞ ከ6 ኪሎ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ የመሬት ፖሊሲ ላይ ያለውን ጥያቄ ለክፍል አስተማሪው የጠየቀ የ12ኛ ክፍል ተማሪ በአንድ አመት እስራት ተቀጣ

በጉራጌ ዞን ቡታጅራ ወረዳ የ12ኛ ክፍል ተማሪ የሆነው አስቻለው ቢራቱ ወርዶፋ የተባለ የማህበረሰብ ሳይንስ ተማሪ የኢኮኖሚክስ አስተማሪውን በሁለቱ ቀደምት ሥርዓቶች ማለትም በንጉሰ ነገስቱና በደርግ ዘመን የነበረው የአገሪቱ የመሬት ፖሊሲ አሁን ሥልጣን ላይ ካለው የኢሃደግ ፖሊሲ በምን እንደሚለይ እንዲያስረዳው ጥያቄ በማቅረቡ "ትምህርቱን አላማ ወደአለው የፖለቲካ ጥያቄ ቀይረሃል" በማለት እንደተከሰሰ እና አንድ አመት ጽኑ እስራት እንደተወሰነበት ኢሳት የተባለው የመጀመሪያው የኢትዮጵያዊያን ነጻ ተሌቪዥን ዘገበ።

እንደኢሳት ዘገባ ምንጭ ክሱን የተመለከተው የቡታጀራ ወረዳ በሃሰት የተዘጋጁ የከሳሽ ምስክሮች የምስክርነት ቃላቸውን ከሰጡ ቦኋላ ተማሪ አስቻለው በአንድ አመት እስራት እንዲቀጣ ፍርድ ቤቱ የመጀመሪያ ወሰኔ አስተላለፈ። በውሳኔው ቅር የተሰኘው ተከሳሽ ፍርዱን በመቃወም ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢጠይቅም ይግባኝ የተባለበት ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በማጽናት የአንድ አመት እስራቱን እንዳጸደቀ ተዘግቦአል።

በለጋ ዕድሜ ውስጥ ያለ አንድ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በትምህርት ገበታ ላይ ለሚያነሳው ጥያቄ እንዲህ አይነት እስራት ሲወሰንበት የመጀመሪያው በመሆኑ የወያኔ የፍትህ ሥርዓት ከጊዜ ወደጊዜ በምን አይነት ዝቅጠት ውስጥ እየተዘፈቀ መምጣትን ያሳያል ያሉ አንድ የህግ ባለሙያ በተለይ ተከሳሽ ለሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ችሎቱ በ500 ብር ዋስ እንዲለቀቅ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ውጥረት ሲበዛበት በልማት ሽፋን ህዝብን የማዘናጋት ፕሮፓጋንዳ ጀመረ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ አባይን በመገደብ የጣና ሐይቅን ሁለት እጥፍ የውሃ መጠን የመያዝ አቅም እንዲኖረው አደርጋለሁ በማለት መግለጫ ማውጣቱ የታወቀ ሲሆን መግለጫው ህዝብን በተስፋ ለመደለል የታቀደ ነው በማለት አስተያየት ሰጪዎች ተናገሩ::

አስተያየት ሰጪዎቹ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በቅድሚያ ኤርትራ ላይ ለመዝመት ቆርጦ መነሳቱን መግለጹ የሚታወቅ ሲሆን ይህ ሃሳቡ ተቀባይነት እንዳጣ ሲገነዘብና ህዝባዊ አመጹ እየተፋፋመ ሲመጣበት በመደናገጥ ላለፈው ሃያ ዓመት ያላስታወሰውን የአባይ ግድብን ስራ አከናውናለሁ ማለቱ ህዝብን የተስፋ ዳቦ የማስገመጫ ፕሮፓጋንዳው ነው ብለዋል::

ቀደም ብሎ በሃይድሮሎጂካል ሳይንስ የማስትሬት ዲግሪ ያላቸውና ከውሃ ልማት ሰራተኝነት በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የተባረሩ አንድ ባለሙያ በስልክ በሰጡን አስተያየት ወያኔ አባይን የመጠቀም ልባዊ አላማ ቢኖረው ኖሮ ላለፉ ሃያ ዓመታት ባልተኛ ነበር፣ ያኔ በ1983 ገና አዲስ አበባ እንደገባ በግምባር ቀደምትነት ከህንጻ ኮስትራክሽን መስሪያ ቤት ጀምሮ ያፈረሰው መስሪያ ቤት የውሃ ልማትን ነበር:: በወቅቱ የውሃ ልማት መስሪያ ቤትን ሲያፈርስ በርካታ የፒኤች ዲ ዲግሪ ያላቸውን ጨምሮ ሃይድሮሎጂስቶች የውሃ መሃንዲሶች በማባረር በደርግ ጊዜ ለውሃ ግድብ መስሪያ ከውጪ ሃገራት ተገዝተው ገብተው የነበሩ መሳሪያዎች በሙሉ እንዲዝጉና ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆኑ ማድረጉ እንዲሁም ጥራት ያላቸውን መሳሪያዎች ደግሞ ወደ ትግራይ ማጉአጉአዙ ይታወሳል ብለዋል::

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ አመጽ በድንገት መነሳቱ አይቀሬ ነው፣ በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች እምቢተኝነትና ግጭቶች መከሰታቸው ቀጥሉአል

በዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በከፍተኛ ሁኔታ ታፍኖ እየተሰቃየ የሚገኘው ግፍና በደሉ ሞልቶ የፈሰሰው የኢትዮጵያ ህዝብ ህዝባዊ አመጽ ድንገት ሊያስነሳ እንደሚችል ታወቀ:: መድረክ በመባል የሚታወቀውና የበርካታ ፓርቲዎች ጥምር ባወጣው መግለጫው ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ህዝብ እየቀረበለት ላለው ጥያቄ አፋጣኝ መፍትሄ ካላመጣ ህዝባዊ አመጽ መነሳቱ እንደማይቀር አስጠንቅቁአል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዜና ኑሮን መቋዋቋዋም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋበት የሄደው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለያዩ ሰበቦች እምቢተኝነቱን እየገለጸ መሆኑም ታውቁአል:: የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ባወጣው ዘገባው የኮምቦልቻ ነጋዴዎች የተጣለባቸውን ግብር አንከፍልም በማለት እምቢተኛነታቸውን እየገለጹ ሲሆን የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት ሆድ አደሮች ለህዝቡ ባቡር ለመዘርጋትና ለኒዩክሊየር ሃይል ማመንጫ ግምባታ የሚውል ገንዘብ ነው በማለት ለማባበል ቢሞክሩም ነጋዴዎቹ የምትሉትን አንሰማቺሁም፣ ህዝቡ የሚበላው ባጣበት ሰአት ከህዝብ ጋር አታጋጩን በማለት እቅጩን የነገራቸው መሆኑ ታውቁአል::

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ አገዛዝ መልእክተኞች ከፍተኛ ተቃውሞ ይጠብቃቸዋል፣ በሰሜን አሜሪካ ዝግጂቱ ተጧጡፎ ቀጥሎአል

የፊታችን ቅዳሜና እሁድ አፕሪል ዘጠኝና አስር ቀን 2011 የትግራዩ ገዢ ጉጂሌ በርካታ ባለስልጣናትን ያካተተ የሉካን ቡድን በሰሜን አሜሪካና ካናዳ በሚገኙ አስራ አራት ከተሞች በመገኘት ስብሰባ ለማከናወን ያቀደ መሆኑ በስፋት ሲዘገብ የቆየ ሲሆን ይህን ስብሰባ የሚቃወሙ በርካታ ኢትዮጵያዊያን በበኩላቸው ዝግጂት እያደረጉ መሆናቸው ታውቁአል::

በአገዛዙ ሆድ አደር ግርማ ብሩ የተጻፈው ደብዳቤ ኢትዮጵያ ከዘመናት የማሽቆልቆል ጉዞ ተላቃ በእድገት ጎዳና ላይ መገስገሱአንና ይህን እድገት በሚቀጥሉት አመታት ኢትዮጵያዊያን እጂ ለእጂ ተያይዘን መስራት ይጠበቅብናል ይላል:: ደብዳቤው በውጪ ሃገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ለሃገራትቸው ልማትና እድገት የተለየ አስተዋጽኦ አላቸው፣ ዴሞክራሲን ለማጎልበትና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን በማፋጠን የህዝባችንን ተጠቃሚነት አስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ በውጪ ሃገራት የሚገኙ ወገኖቻችን ሚናቸውን ይጫወቱ ዘንድ አስፈላጊውን ሁሉ አመቻችተናል::በማለት ትውልደ ኢትዮጵያዊያኑ በትራንስፎርሜሽን እቅዱ እንደሃገር ውስጥ ባለሃብቶች ሁሉ ውይይት ሊያደርጉበት ይገባል ይላል::

የኢትዮጵያን ህዝብ በችጋር አለንጋ እየገረፈ ነገር ግን ጥቂት የገዢው ቡድን አባላትና ሆድ አደሮችን ብቻ በዝርፊያ እያበለጸገ ያለው የወያኔ አገዛዝ፣ ኢትዮጵያዊያን ሃሳባቸውን በነጻነት እንኩን መግለጽ እንዳይቺሉም ሆነ ከነጻ ብዙሃን መገናኛ መረጃ እንዳያገኙ አፍኖ የያዘው ዘረኛ አገዛዝ ከሃገር አልፎ በውጪ ሃገራት ያለውን ህዝብ ለማሞኘት የሚያደርገውን ሙከራ ለማክሸፍ ኢትዮጵያዊያኑ ከመቸውም በላይ ዝግጂት ማድረጋቸውን ለዝግጂት ክፍላችን የደረሰ መረጃ አሳይቱአል:: (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# በአገራችን ነጋዴ ላይ እየደረሰ ያለው ውርደት እና ስልታዊ ዘረፋ ማብቂያ ደርሷል!!!

መለስ ዜናዊ ለዘረኛ አገዛዙ ወገንተኛ ያልሆኑ የፕሬስ፣ የሙያ ማኅበራትና የፓለቲካ ድርጅቶችን እያዳከመ መጥቶ በአሁኑ ሰዓት ትኩረቱን በንግዱ ማኅበረሰብ ላይ ጥሏል።

እንደ መንገድና ህንፃ ግንባታ፤ ትራንስፓርትና ማጓጓዣ፤ አስመጪና ላኪ የመሳሰሉ ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኙ የንግድ መስኮች ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል ሁኔታ በመለስ ዜናዊ በሚመራው የማፍያ ቡድን ቁጥጥር ስር ከዋሉ ዓመታት ተቆጥረዋል። እነዚህ የወያኔ እና የአፍቃሪ-ወያኔ ንግድ ተቋማት የካፒታልም ሆነ የገበያ ችግር የለባቸውም። በግብርና ታክስ፣ በመዋጮ፣ በቢሮክራሲ ውጣ ውረድ አይጉላሉም። ሁሉ በእጃቸው፤ ሁሉ እደጃቸው ነው። ለዘረፋቸው ማጠናከሪያ “ልማታዊ ድርጅቶች” የሚል መለያ ተሰጥቷቸው የአገዛዙ የኢኮኖሚ እንክብካቤ ብቸና ተጠቃሚዎች ናቸው። በዚህ ልዩ ጥቅም መሠረትም የመንግሥት ጨረታዎች የሚሰጡት ለእነሱ ነው፤ የእርዳታ እህል የሚመላለሰውም በእነሱ ነው። የውጭ አገራት የቴክኒክ ድጋፍ ከተገኘም ተጠቃሚዎች እነሱ ናቸው። አገዛዙ በእነሱ፤ ለእነርሱ የቆመ ነው።

በአንፃሩ ከወያኔ ጋር ያልወገነ በራሱ ጥሪት የሚንቀሳቀስ ነጋዴ አለ። ከዚህ ውስጥ በቁጥር እጅግ የበዛው በአነስተኛ ጥሪት ባቋቋማት ንግድ የራሱንና የቤተሰቦቹን ጉልበት ተጠቅሞ በጥረቱ ራሱንና ቤተሰቡን ከረሃብና ከልመና ለማውጣት የሚፍጨረጨር ለፍቶ አዳሪ ነው። ይህ የነጋዴው ክፍል በሥራ ፈጣሪነቱ መሞገስ፣ መበረታታትና በአርዓያነት መታየት ነበረት።

በመለስ ዜናዊ አገዛዝ እየሆነ ያለው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። በዛሬይቷ ኢትዮጵያ ከወያኔ ሹማምንት ጋር ሳይወዳጁ የንግድ ሥራ መጀመር ፍም ላይ እንደመራመድ ነው። የተቆለለ የግብር እዳ፤ ማለቂያ የሌላቸው መዋጮዎች፤ ለትንሽ ለትልቁ የሚጠየቀው ጉቦና ውጣውረዱ ነጋዴውን ማኅበረሰብ እጅግ አስመርሮታል። አንዳችም የንግድ ችሎታም ሆነ የምጣኔ ሃብት እውቀት የሌላቸው ሰዎች ባስቀመጡት ዋጋ ካልሸጥክ እየተባለ ነጋዴው እንዲከስር፤ ቤተሰቦቹም እንዲበተኑ እየተደረገ ነው። ካድሬዎች ሸቀጥ በጅምላ በማይገዛበት ዋጋ በችርቻሮ ሸጡ እያሉ ሻጭና ገዥ ሽሪኮች በመሆን ፋንታ እንደ ጠላት በጥርጣሬ እንዲተያዩ እየተደረገ ነው። ነጋዴው በጥረቱ ያፈራውን ንብረትም ያለአንዳች የህግ አግባብ በጉልበት ይነጠቃል። በርካታ ነጋዴዎች ሰርቼ-ልደር ባሉ በግብር ሰበብ እስር ቤት ይወረወራሉ።

ነጋዴው ወገናችን እየከፈለ ያለ የክብር ዋጋም የትየለሌ ነው። ከመለስ ዜናዊ እስከ እስከቀበሌ ሹም ነጋዴን መስደብና ማዋረድ የስልጣኔ ምልክት አድርገውታል። የብዙ ቤተሰብ አስተዳዳሪ የሆኑ ለፍቶ አዳሪ ነጋዴ አዛውንት የእርዳታ እህል በሚሸጥ የመንደር ካድሬ ሳይቀር “ስግብግብ” ተብለው ተሰድበዋል፤ እየተሰደቡም ነው። በርካታ አዛውንት ነጋዴዎች በቤተሰቦቻቸው ፊት “ሌባ” እየተባሉ ተዋርደዋል። ሌባ ለፍቶ አዳሪን “ሌባ” ብሎ ሲሰድብ ህመሙ ጥልቅ ነው።

ይህ ወደ የት ያመራናል?

መልሱ ግልጽ ነው። ይህ ጥቃት ወደ ህዝባዊ እምቢተኝነት ብሎም ወደ ነፃነት ይመራናል። ግፍ ሲበዛ ህዝባዊ እምቢተኝነትን ይወልዳል። ህዝባዊ እምቢተኝነት ደግሞ ነፃነትን ያቀዳጃል። የአገራችን ነጋዴ የወያኔ የወተት ላም መሆኑ ማብቂያ ጊዜ ደርሷል።

ነጋዴው ሲነሳ አገር ባንድነት ይነሳል። ቅርቦቻችን በሆኑ አገራትም የታየው ይኸው ነው። ሰሜን አፍሪቃንና መካከለኛው ምሥራቅ አዳርሶ ወደ አገራችን በመገስገስ ላይ ያለው ህዝባዊ አብዮት የተጀመረው በአነስተኛ ጥሪት ፍራፍሬ ሲቸረችር በነበረ አንድ ወጣት ነው።

ዛሬ ስሙ በመላው ዓለም የታወቀው ቱኒዚያዊው መሃመድ ቦዛዚ የሃያ አራት ዓመት ወጣት የነበረ ሲሆን ከቱኒዝ 150 ኪሜ ርቃ በምትገኝ ሲዲ ባውዚድ በምትባል ከተማ አትክልትና ፍራፍሬ እየሸጠ ይተዳደር ነበር። የከተማው ፓሊሶች በተደጋጋሚ እቃውን ዘረፉት፣ ሰደቡት፣ ደበደቡት። ወጣቱ መሃመድ ቦዛዚ የመነገጃ ቦታ ለማግኘት እከተማው ማዘጋጃ ቤት ተመላለሰ፤ ግን ከአገሪቱ አምባገነን ቢን ዓሊ ወገን አልነበረምና የሚሰማው አላገኘም። በዚህ ተደጋጋሚ ግፍ የተማረረው መሃመድ ቦዛዚ ቤንዚን በራሱ ላይ አርከፍክፎ ክብሪት ጫረ። መሃመድ ቦዛዚ ከሁለት ቀናት በኋላም ህይወቱ አረፈች። ዜናው በፍጥነት ተሰራጨ። የእርሱ መስዋዕትነት አገሩን ነፃ አውጥቶ ጎረቤቶቻችንን ሁሉ አዳርሶ እኛም ዘንድ እየመጣ ነው።

የወያኔ ሹማምንት ገነትን ምድር ላይ እንደሚገነቡ ቃል መግባት ይችላሉ። መዋሸት ለምደውባቸዋል። የነጋዴው ማኅበረሰብ ከእንግዲህ ይህንን የሚሰማበት ጆሮ የለውም። በቅርቡ በኮምቦልቻ ከተማ የወያኔ ሹማምንት ነጋዴዎችን ሰብስበው “የባቡር መንገድ እናሰራለን፤ የኑዩክለር ኃይል ማመንጫ እናስተክላለን” ሲሉ “እኛ ችግራችን የእለት እንጀራችንን ማግኘት ነው” ያሉት አዛውንት በወያኔ የቅዠት እና በእውነተኛው ዓለም መካከል ያለውን ልዩነት አጉልቶ ያሳየ፤ አርዓያነቱ የጎላ አነጋገር ነው።

በመለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራይ ገዢ ጉጅሌ የራሱ ነጋዴዎች አሉት። ጉጅሌው የሚፈልገው ከችርቻሮ እስከ ጅምላ፤ በኮንስትራክሽን፣ በማምረቻ፣ በፋይናንስ ... በሁሉም መስኮች ያለው የንግድ ሥራ ሁሉ በቡድኑ አባላት እንዲያዙና ሌላው የበይ ተመልካች እንዲሆን ነው።

ይህ ብቻም አይደለም፤ ዛሬ ነጋዴው የበይ ተመልካችነትም ተነፍጎ ኪሳራ ውስጥ እንዲገባ እየተደረገ ነው። የአንገራገረው ደግሞ በግብር እዳ ስም ወደ ወህኒ እየተወረወረ ነው። መቼ ነው ነጋዴው ማኅበረሰብ “ጥቃት በቃኝ!” የሚለው? መቼ ነው በመሃመድ ቦዛዚ የተለኮሰው የነፃነት ችቦ ኢትዮጵያዊያን ነጋዴዎች የሚቀበሉት?

ጊዜው ደርሷል!!!! የሁላችን የጋራ ጠላት በሆነው በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ የምንነሳበትና ነፃነታችንን የምንቀዳጅበት ቀን ደርሷል!!! በዚያ ቀን በጋራ መቆም አለብን። ትግላችን ቀናትን ሳይሆን ሳምንታትን ምናልባትም ወራትን ይፈጅብን ይሆናል። ድል ሳናደርግ ወደ ቤት መመለስ ግን የለም።

**በየቋንቋዎቻችን “በቃ!!!” እንበል!!!!**

**በቃ!!! ገዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጉደስ!!!**

## በአገሪቱ ውስጥ እየተስፋፋ በመጣው ህዝባዊ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አላማ ይዘው እየተንቀሳቀሱ ነው” በማለት የሚወነጀሉት ሁለቱም አገሮች ወያኔ ጻረ ደርግ ትግል ያደርግ በነበረበት ወቅት ከፍተኛ የሆነ የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍ ምንጮቹ የነበሩ መሆናቸውን የሚያውቀው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ የከትናንትና ወዲያ ንግግሩን የሰማው በሰውየው መረበሽ እጅግ እየተገረመ እንደሆነ የግንቦት 7 ዘጋቢ ያነጋገራቸው አንዳንድ የፖለቲካ ሰዎች ገልጸዋል።

መለስ ዜናዊ በዚህ የተስፋ መቁረጥ የፓርላማ ንግግሩ፤ ለአመታት በህዝባችን ላይ ሲፈጽም ለኖረው ሰቆቃና በአገራችን ዘላቂ ጥቅም ላይ ለፈጸመው ወንጀል የራሱንና ከጫካ እስከ ሚኒልክ ቤተመንግሥት አብረዉት የነበሩት ግብረ አበሮቹ ሲሰሩት የኖሩትን ወንጀል ሙሉ በሙሉ በመሸፋፈን የህዝባቸው የአመታት ሰቆቃ መራራ የሆነ ጻረ ወያኔ ትግል ውስጥ የከተታቸውን የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና አባላት ላይ ዛቻ እና ድንፋታ ሲያርከፈክፍ ታይቶአል። መለስ ዜናዊ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማስፈራራት እና ለማሸማቀቀ ይደነፋ በነበረበት በያንዳንዱ ንግግሩ በተለያየ አነስተኛ ጥቅማ ጥቅም ተታለው ወያኔ በአገራቸውና በህዝባቸው ላይ እየፈጸመ ያለውን የጥፋት ፖሊሲ በማስፈጸማቸው ታማኝነት አግኝተው በምርጫ ሽፋን ፓርላማ የተጠራቀሙት አባላቶቹ ሳይቀር ሳቃቸውን መቆጣጠር አቅቶዋቸው ሲያሽካኩ እንደነበረ የሸንጎን ውሎ በምስል ያቀረበው የወያኔ ተሌቪዝን ለህዝብ ዕይታ አቀርቦታል።

በተለይ ህዝባዊ አብዮት ሊነሳ ይችላል በሚል ስጋት ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በጅምላ እየታሰሩ ባሉት የ ኦሮሞ ተወላጆች ላይ በመሰረተው ክስ “ለሽብር ተግባር እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን በማወቃችን በቁጥጥር ሥር ያዋልናቸውን ሽብርተኞች አባላቶቼ ናቸው በማለት የመድረክ አባል ድርጅቶች ሃላፊነት በመውሰዳቸው ማንነታቸውን በግልጽ እንድናውቅ ዕድል ሰጥቶናል” በማለት መድረክን ሲያስጠነቅቅ በተለይ “አንድነት” አመጽንና ህዝባዊ ተቃውሞን በማቀናጀት ተግባር ላይ ተሰማርቶ ስለሚገኝ፡”እየሰሩት ላለው ሥራ ዋጋ እንደሚከፍሉ ሊያውቁት ይገባል በማለት ዝቶአል።

በቱኒዚያ የተቀሰቀሰውና ሰሜን አፍሪካን አቋርጦ መካከለኛ ምስራቅ አገሮች ውስጥ ያሉትን አምባገነን መሪዎች እያርበተበተ በመሄድ ላይ ያለው ህዝባዊ አብዮት “ልማት አምጥተንልሃል ፤ ኑሮህን አሻሽለንልሃል ፤ መንገዶችንና ግድቦችን ከመገንባት አልፎ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ በየአገሮቹ ውስጥ እንዲያብቡ አድርገናል” በማለት ህዝባቸውን ሲደልሉ እና ለራሳቸው ረጅም የስልጣን ዕድሜ በማመቻቸት የየአገራቸውን ሃብት ሲዘርፉና ሲመዘብሩ የኖሩትን የመለስ ዜናዊ አይነቶቹን ዕድሜ በአጭር ቀናት እንዳሳጠረ ይታወቃል።

## የወያኔ የግፍ አገዛዝ ያበቃ ዘንድ ህዝብ ለነጻነቱ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በሚወስደው መንገድ ላይ ባለው ከአንድ አመት በፊት በተሰራው የአፍንጮ በር ድልድይ ላይ “ሞት ለወያኔ “ የሚል መፈክር በትላልቁ ተጽፎ በመገኘቱ የወያኔ ጸጥታ ሰራተኞች ከጠዋቱ 2 ሰዓት ተኩል ላይ በቦታው ተገኝተው ለማጥፋት ሲታገሉ እና የተጻፈበት ጥቁር ቀለም እንዳይታይ ድልድዩን በጥቁር ቀለም ሲቀቡት እንደተስተዋለ ድርጊቱን በአይን የተመለከተ የግንቦት 7 ተባባሪ ዘጋቢ ለዝግጅት ክፍላችን በኢሜል ገልጾአል።

የወያኔ ጸጥታ ሰራተኞች መፈክሩን ለማጥፋት በሚታገሉበት ወቅት ድልድዩን በእግርና በመኪና በማቋርጥ ላይ የነበሩ የከተማው ነዋሪዎች ከፊሉ በሳቅ ከፊሎ ደግሞ በማሾፍ “ለምን ቀለም ታባክናላችሁ” በማለት ሲናገሩ መደመጣቸውን እኚሁ ተባባሪ ዘጋቢያችን ከላከልን ሪፖርት ለመረዳት ተችሎአል። የአፍንጮ በር ድልድይ በርካታ እግረኞችና ባለመኪናዎች የሚጠቀሙበት እንደመሆኑ የጸጥታ ሰራተኞቹ መፈክሩን ለማጥፋት በቦታው በተገኙበት በዚያን ሰዓት በርካታ ሰዎች ወደሥራ ለመሄድ ድልድዩን የሚያቋርጡበት ሰዓት ስለነበር የብዙዎች ቆም ብለው ድርጊታቸውን በአግራሞት መመልከት ከፉኛ እንዳስደነገጣቸው እና ህዝብ ይሰነዝር ለነበረው የብሶት አስተያየትም ጆሮ ለመስጠት እንዳልቻሉ ተያይዞ የደረሰን መረጃ አመልክቶአል። የቱኒዚያ ህዝባዊ አመጽ ወደ ግብጽና ሌሎች የሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ ከተዛመተ ወዲህ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተሰማሩ ፖሊሶች እምነት ያጣው የትግራይ ገዥ ጉጇሌ ሲቭል ልብስ የለበሱ ትግሪኛ ተናጋሪ የህወሃት አባላትን ለጥበቃ ሥራ በተደራቢነት ማሰማራቱን የግንቦት 7 ዘጋቢ ታማኝ ምንጮችን ዋቢ በማድረግ ገልጾአል።

## የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር በ1996 ዓ.ም ባዘጋጀው ርዕይ 2020 የውይይት መድረክ የቀረበ (በዶ/ር ታደሰ ብሩ)

### ጽሁፉ የያዛቸው በርካታ ቁም ነገሮች ስላሉ በዚህ ጋዜጣ በተከታታይ ለማቅረብ ችለናል (ክፍል 4 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ )

ሆኖም ከሚከተሉት አንዱ ወይም ጥቂቱ መሟላት ለእንዲህ ዓይነቱ ድርድር ይጋብዛሉ ተብሎ ይታመናል::

1. ግጭት ቢነሳ ከአጠቃላይ ውድመት በስተቀር የአንድ ወገን ድል እንደማይገኝ በሁሉም ወገኖች ዘንድ ሲታመን ማለትም ተፋላሚዎች በኃይል ሲመጣጠኑ፤
2. እያንዳንዱ ተደራዳሪ በድርደሩ የራሱን ሕልዉና ማስጠበቅ ሲችል ከሥልጣንም ድርሻ እንደሚኖረው ሲያረጋግጥ፤
3. በተራዘመ የርስ በርስ ጦርነት ምክንያት የሕዝቡ «አብዮታዊ» ስሜት ሲላሽቅና የአርበኝነት ወኔው እያደር ሲከዳው፤
4. ልሂቃኑ በረዥም ጊዜ የትግል ልምዳቸው፣ በበሰለ አመራራቸው ወይም እንደ ተረት በሚወራላቸው ጀግንነታቸውን ምክንያት በተከታዮቻቸው ዘንድ ከፍ ያለ እምነትና ክብር ሲጎናጸፉና በዚህም ምክንያት ከጠላት ጋር ቢደራደሩ በብልህነት እንጂ በከሃዲነት እንደማይቆጠርባቸው ሲሰማቸው፤
5. አንዱ ወገን ለጊዜው ኃያል መሆኑ ቢሰማውም እንኳን ጦርነቱ ቀጥሎ ምናልባት ቢሸነፍ እጅግ ዋጋ የሚሰጠውን ሌላ ጉዳይ የሚያጣ መሆኑን፤ ዛሬ ጉልበቱ ሳይደክም ቢደራደር ግን ያ ከፍተኛ ዋጋ የሰጠውን ጉዳይ ማስጠበቅ እንደሚችል ሲያምን - ለምሳሌ በደቡብ አፍሪቃ ነጮች የተጠበቀላቸው የባለሙሉ ዜግነት መብት፣ የእንግሊዝ የዘውድ ክብር፣ የፖላንድ ኮሚኒስቶች እስከዛሬም ያላቸዉ ተሰሚነትና ቦታ፤ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት (በአድዋ ጦርነት ማግስት በአፄ ሚኒሊክና በጣልያን መካከል በተደረገዉ ስምምነት)፣ … በዚህ መሰሉ ድርድር የተጠበቁ እሴቶች ናቸው::

በሌላ በኩል ግን ዓለም-አቀፍ ተፅዕኖ ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ድርድሮች መፈጠር ያለዉ ሚና ደካማ ነዉ:: የተራዘመ ዓለም-አቀፍ ጫና ቢደረግባቸዉም ፋይዳ ያለዉ ስምምነት ላይ መድረስ ያልቻሉ ልሂቃን ብዙዎች ናቸዉ:: ከዚህ የምንረዳዉ አንድ ተጨማሪ ሃቅ አንጀት የሚያራሩ የሰላም ንግግሮች የሚደመጥባቸው ዓለም-አቀፍና አገር-አቀፍ ጉባኤዎች፣ የሰላም ጉዞዎች፣ ሰላማዊ ሰልፎች፣ መዝሙሮች፣ ፖስተሮች፣ …፣ወዘተ፣ ወዘተ፣ ተፋላሚ ልሂቃንን ተከታይ በማሳጣት ረገድ ሊኖራቸው ከሚችል የረዥም ጊዜና የዙሪያ ጥምጥም ደካማ ተጽዕኖ በስተቀር ወይም በሰላም ስም ለሚነሳ ƒስተኛ ወገን አመቺ ሁኔታን ከመፍጠር ሌላ ተፋላሚዎችን ወደ ድርድር ጠረጴዛ በማቅረብ ረገድ እጅግም ተግባራዊ ፋይዳ የሌላቸው መሆኑን ነዉ:: ለእንዲህ ዓይነቱ የሕዝብ ጥሪ እያንዳንዱ የልሂቃን ቡድን እሱ ሰላም ወዳድና ድርድር ፈላጊ ሲሆን ተቃዋሚው ወገን ለድርደር ያልተስማማ በመሆኑ ሳይወድ በግድ አማራጭ በማጣቱ የሚዋጋ መሆኑን በቁጭትና በሀዘን በመግለጽ ይመልሳል:: ተፈላሚዎች ራሳቸው ሰላምን ከሚማፀነዉ ሕዝብ ጋር ለሰላም የዘመሩበት አጋጣሚ ለቁጥር እስኪያታክት ብዙ ነው:: ይህ ብቻም አይደለም:: ልሂቃን በመሠረቱ ከሚወክሉት የሕብረተሰብ ክፍል የላቁ አባላት በመሆናቸው ሁሉን አውቅነት የሚያጠቃቸው በመሆኑ ከገለልተኛ ሊቃውንትና ከአገር ሽማግሌዎች የሚቀርብላቸውን ምሁራዊና አባታዊ ምክር ከልብ አያዳምጡም::

ከላይ የጠቀስኳቸው አይነት ብርቅዬ ድርድሮች ሁለት አስደናቂ ባሕርያትን ይዘዋል:: አንደኛ፣ የመጀመሪያዎቹ ዙሮች ውይይቶች ቁጥራቸው በጣም ጥቂት በሆኑ ልሂቃን (እንዲያዉም ብዙ ጊዜ በሁለቱ አዉራ ተፋላሚ ልሁቃን ብቻ) ተሳታፊነት በሚስጥር ወይም በከፊል ምሥጢር መከናወናቸው ነዉ::ከመጀመሪያዎቹ ምስጢራዊ፣ «የልብ-ከልብ» ዉይይት በኋላ ነዉ ሽምጋዮች ያሉበት እሰጥ አገባ የበዛበት ድርድር የሚካሄደዉ:: የመጀመሪያዎቹ ዙሮች ፈጣን፤ የኋለኞቹ ደግሞ ጎታታ፣ ናቸዉ::

ሌላው አስደናቂ ጉዳይ ደግሞ እጅግ የተለያዩ ርዕዩተ-ዓለሞችን የሚያራምዱ ተፋላሚ ልሂቃን አንድ አይነት ርዕዩተ-ዓለም ካላቸው ልሂቃን የበለጠ ተገናኝቶ የመደራደር ዝንባሌ ያላቸው መሆኑ ነው:: ይህ ብዙዎች ማመን ቢያስቸግራቸዉም ዕዉነት ነው:: ትናንሽ ልዩነቶች ከትላልቅ ልዩነቶች ይበልጥ በቀላሉ ይከራሉ::

**ለምንድነው ዘላቂ ሰላምና ልማትን ለማምጣት ዲሞክራሲ የተሻለ አማራጭ ነው የሚባለው?**

ሰላም የሰፈነበት ሥርዓትና ሌሎችም ማህበራዊ ምርቶች /public goods/ ከሌሉ ማኅበረሰብ በአጥጋቢ ሁኔታ ሥራዉን መከወን አይችልም:: የሽብርና ዘረፋ ሰለባዎች የሚያጡት ለፍተው ያፈሩትን ሃብት ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም ሃብት የማፍራት ፍላጎትንም ጭምር ነው:: ስለሆነም ሥርዓት አልበኝነት ለልማት ተመራጭ መሆን አይችልም:: ሁሉንም የማኅበረሰቡ አባላትን የሚጠቅም ስለሆነ ብቻ ሰላማዊ ሥርዓት በሕዝቦች የጋራ ስምምነት ይሰፍናል ማለት ግን የዋህነት ነው:: ሰላም ከፍተኛ ወጪና መስዋትነትን ይጠይቃል ውጤቱ ግን የጋራ ነው:: የሰላም ተጠቃሚ ሁሉም ነው፤ ወጪው ግን የግል ነው:: ስለሆነም እያንዳንዱ «ብልጥ» ሌላው ሰው ታግሎለት ሰላምን እንዲያመጣለት በመጠበቅ የግሉን ኪሳራ ሲቀንስ በሁሉም ሰው የሚወደደው ሰላም እንደተናፈቀ ይቀራል:: የሰዎች ኪሳራ የመቀነስ /cost minimizing/ ባህሪይ ለምርጫ ጥቂት ሰዓታት ለማጥፋት ምን ያህል እንደምንሰስት በማየት ብቻ እንኳን መታዘብ ይቻላል::

ዘላቂ ሰላምና ልማት በሕዝብ የጋራ ውሳኔና ፍላጎት የሚወሰን ቢሆን ኖሮ በዓለማችን ላይ ሰላምም ልማትም ባልኖሩም ነበር:: በሚፈለገዉ መጠን ባይሆንም ሁለቱም በዓለማችን ላይ አሉ:: ይህም ሊሆን የቻለው ከሰላም የሚገኘው ጥቅም በግል ከሚያስወጣው ወጪ እጅግ በላይ የሆነለት አካል ስላለ ነው::

እዉቁ ኢኮኖሚስት ማንክዩር ኦልሰን ተረት በመሰለ ጣፋጭ ትረካ ነው ይህንን ያብራራው:: ዘላን ወንበዴዎች /roving bandits/ ነጥቀው ይሮጣሉ፤ መቼ እንደሚመለሱ አይታወቅም:: እነዚህ ወንበዴዎች ነጥቀው በሮጡ ቁጥር የማኅበረሰቡ ሃብት የማፍራት ፍላጎት ስለሚዳከም በሚቀጥለው ዙር የሚዘርፉት ነገር እያነሰባቸው ይመጣል:: ቀን ባለፈ መጠን ነጥቆ መሮጥ ራሳቸውን እንደሚጎዳቸዉ ይገነዘቡና ከተዘዋዋሪ ወንበዴነት ወደ ቋሚ ወንበዴነት /stationary bandit/ ይቀየራሉ:: ለንጥቂያቸዉ ሥርዓትና ልክ ያበጁለታል፤ ስሙን «ግብር» ይሉታል:: ማኅበረሰቡንም፣ ራሳቸውንም፣ ከሌሎች ተዘዋዋሪ ወንበዴዎች ይከላከላሉ:: ይህ ሥርዓት ከሥርዓት አልበኝነት በጣም የተሻለ፤ የቅሚያዉ መጠንም አስቀድሞ የሚታወቅ ከመሆኑ ጋር ማኅበረሰቡ ለሚከፍለው ተመጣጣኝም ባይሆን የሚያገኘው ጥቅም ( ሰላምና ሌሎችም public goods) ስላሉ ምርት ይጨምራል፤ ዕድገትም ይኖራል::

ይሁን እንጂ አምባገነን ሰፋሪዎች በተደላደሉ መጠን ፍጆታቸው እየናረ መሄዱ ፈጽሞ የማይቀር ነው:: ለጦር ሠራዊቱ፣ ለቤተ-መንግሥቱ፣ ለቤተ-መቅደሱ፣ ለማሰልጠኛው፣ ለመታሰቢያ ኃውልቶች ግንባታ፣ ለመሰብሰቢያ አዳራሾች ግንባታ፣ ለክብረ-በዓላት ማስጌጫ፣ በዉጭ አገር ባንኮች ለሚከማቸዉ «መጠባበቂያ» ሂሳብ (ሞቡቱ 8 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ክምችት ነበረዉ ይባላል) ለአንባገነኖቹና ለቤተሰቦቻቸዉ የክብር ልብሶችና ጌጦች መግዣ (ኢሜልዳ ማርቆስ 3000 ጥንድ ጫማዎች ነበሯት)፣ ወዘተ፣ የሚጠየቀው ወጪ በጨመረ ቁጥር ሕዝቡ በታክስ አሊያም በሌላ መንገድ እንዲከፍል ስለሚገደድ ሥርዓት በመስፈኑ ምክንያት አንሰራርቶ የነበረው የሥራ ፍላጎት እንደገና ያሽቆለቁላል:: የሰፋሪ መንበዴዎችን የሃብት ማጋበስ፣ ምኞትና እዩልኝ ፋላጎቶችን ማርካት አይቻልም::

ሰፋሪ ወንበዴዎች /stationary bandit/ ከፍጆታቸው ከአቅም በላይ መናር በተጨማሪ ሌሎችም ችግሮች አሉባቸው:: አንዱ የሥልጣን ሽግግር /succession/ ችግር ነው:: ልሁቁ ወንበዴ በደከመ ወይም ባረጀ ጊዜ በማን እንደሚተካ ግልጽ መመሪያ ስለማይኖር ከአንድ አምባገነን ወደሌላኛው አምባገነን መሸጋገሪያ ላይ ብጥብጥና አለመረጋጋት ይኖራል:: ስለሆነም በዚህ መንገድ የሚመጣው ሰላም ከአንድ ሰው የስልጣን እድሜ በላይ የመቆየቱ ነገር እጅግ በጣም አጠራጣሪ ነው:: ይህ ጥርጣሬ ራሱ የረዥም ጊዜ ኢንቬስትመንትን የሚገታ የዕድገት ማነቆ ነው::

ንጉሳዊ ሥርዓትም ቢሆን ከሥልጣን ውርስ ችግር ሙሉ በሙሉ የነፃ አይደለም:: የነገሥታቱ ፍጆታ ደግሞ እንደአምባገነኖቹ ሁሉ አቅምን ያገናዘበ አይደለም:: የአለም ታላቅ ቤተመንግሥቶችና ቤተ-መቅደሶች የተገነቡት በነገሥታት መሆኑን ማስታወስ ይበቃል::

ንብረት በግል የመያዝ መብት ያለመንግሥት ሊከበር አይችልም:: ወገናዊ ያልሆነ የፍትህ ሥርዓት ከሌለ ደግሞ ውሎች አይረጉም፤ ቃልኪዳኖች አይከበሩም፤ በሰዎችና ተቋማት መካከል መተማመን ይጠፋል:: ይህ ሁሉ ዕድገትን ያቀጭጫል::

አምባገነኖች የሰብዓዊ መብቶችን ማክበር፤ ለግል ንብረቶች ሙሉ ዋስትና መስጠትና ወገናዊ ያልሆነ የፍትህ ሥርዓት ማስፈን አይቻላቸውም:: እነዚህ ደግሞ ከሌሉ ነፃ የሆነ ንግድና የካፒታል ዝውውር አይኖርም:: ሰዎች ንብረቶቻቸውና ውሎቻቸውን እንዲጠበቁላቸው የሚፈልጉትን ገና ሥልጣን ላይ ካልወጡት ጉልበተኞች ብቻ ሳይሆን ሥልጣን ላይ ካለው ጉልበተኛው ማለትም ከመንግሥትም ጭምር ነው:: እንዲያውም በጣም የሚያስፈራው ኃይል መንግሥት ነው::

ለፈጣን ዕድገትና ለዲሞክራሲ መስፈን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች በመሠረቱ አንድ ናቸው:: ነፃነት፣ ሰላምና ውሎችን ማስጠበቅ የሚችል እና ራሱን የሚቆጣጠር መንግሥት:: ለተፋጠነ ልማት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲቻል መንግሥትን መቆጣጠር የሚያስችል የአስተዳደር ሥርዓት ያስፈልጋል:: ይህ ደግሞ ዲሞክራሲ ነው:: ዲሞክራሲ ሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈጻሚዉ፣ ሕግ ተርጓሚዉ እና ነፃው ፕሬስ እርስ በርስ እየተደጋገፉ፣ እየተጠባበቁና እየተራረሙ እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል::

ለዚህም ነው ካፒታል (ማለትም ገንዘብ፣ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል፣…፣ ወዘተ) በአምባገነኖች ከሚገዙ አገሮች ዲሞክራሲ ወደ ሰፈነባቸዉ አገሮች የሚፈልሰው:: አምባገነኖች ራሳቸዉ ከገዛ ራሳቸዉ አገር ወይም እነሱን የመሰለ ሌላ አምባገነን ከሚገዛዉ አገር ይልቅ ለሃብታቸዉ ማስቀመጫነት የሚመርጡት ዲሞክራሲያዊ አገሮችን ነዉ:: የዚህ ሁሉ ድምር ዉጤት የካፒታል ፍልሰትን ከድሃ ወደ ሃብታም አገሮች እንዲሆን አድርጎታል::

(ክፍል 5 ሳምንት ይቀጥላል)

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ህዝባዊ አመጹን ሊያነሱ ይችላሉ ያላቸውን ወጣቶች የገንዘብ ጉርሻ እየሰጠ ነው

የዘረኛውና አምባገነኑ የትግራይ ገዢ ጉጂሌ መርዘኞች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጭንቀት ፈጥሮ እንደ እብድ የሚያደርጉትን እያሳጣቸው ያለውን ህዝባዊ አመጽ በመፍራት፣ በአዲስ አበባ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች ለሚገኙ ወጣቶች የገንሽዘብ ጉርሻ መስጠት መጀመራቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ::

የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አስገራሚና መሳቂያ የሚባሉ የተደነባበሩ ተግባራትን እያከናወኑ ሲሆን ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ ድህነት የተስፋፋባቸው በተባሉት የአዲስ ከተማ እና የቂርቆስ ክፍለ ከተሞች ውስጥ ለሚገኙ "አማራጭ ያጡ" የሚል አዲስ ስም ለተሰጣቸው ወጣቶች አምስት ሺሕ ብር በነፍስ ወከፍ እየሰጡ መሆኑን ዘጋቢያችን ከላከልን ዘገባ ለማወቅ ተቿሉአል:: ወጣቶቹ ይህን ገንዘብ ለመውሰድ የሚሠሩትን ሥራ ዐይነት እና አድራሻቸውን በሚሰጣቸው ፎርም ላይ እንዲያስቀምጡ እንደሚደረግና ብሩን ለማግኘት በዚያው ቀበሌ ነዋሪ የኾነ ወይም ከአጎራባች ቀበሌ መታወቂያ ያለው ሰው ዋስ በመኾን ሊያስጣቸው ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አሳይቱአል።

ዘጋቢያችን ዘረኛውና መርዘኘው አገዛዝ የጀመረውን አዲስ ተራ የሆነ መደለያ በሚመለከት አስተያየታቸውን እንዲሰጡት ያነጋገራቸው አንዳንድ ወጣቶች እንደተናገሩት አገዛዙ ይህን አዲስ አዲሱን ስትራቴጂ መጠቀም የፈለገው በሥራ ማጣት እና በብር የመግዛት አቅም መዳከም ምክንያት ኑሮን መቁአቁአም ያቃተው ወጣት ድንገተኛ የሆነ ሕዝባዊ ዐመፅ እና ንቅናቄ እንዳያስነሳ በመስጋት የተፈጠረ "ጊዜያዊ ማስተንፈሻ" ነው ብለዋል። ከጥቂት ጊዜ ወዲ ወያኔ እየተከተለ ያለው ግብታዊነት ያለው አሠራርና ድለላ ከህዝብ አይን የተሰወረ እንዳልሆነ፣ እነኝህ ወጣቶችም የሆዳቸውን በሆዳቸው አድርገው ለጊዚያዊ ችግራቸው ገንዘቡን ይቀበሉ እንጂ ማንም ኢትዮጵያዊ ልቡን ለወያኔ ይሰጣል ማለት የማይታሰብ ነው ብለዋል:: አስተያየት ሰጪዎቹ መርዘኛ የሆነው አገዛዝ ኢትዮጵያዊያንን በደካማ ጎናቸው እየገባ ማዳከም ዛሬ የጀመረው ተግባር ሳይሆን የቆየ ነው ካሉ ቦኋላ አሁንም እኒህን ወጣቶች በዛሬው የአገሪቱ የዋጋ ግሽበት ምንም የረባ ነገር ለመግዛት የማያስችል ገንዘብ በማከፋፈል አይቀሬ ነው የተባለው ህዝባዊ አመጽ የፈነዳ ዕለት በጸረ ወያኔ ጎራ ቆመው ለነጻነታቸው ከህዝቡ ጎን እንዳይቆሙ ለመደለል የታለመ ሴራ ነው ብለዋል:: ቀጥለውም በተለይም ወጣቶቹ አድራሻቸውን እንዲያስመዘግቡና ዋስም እንዲያቀርቡ እየተደረገ ያለው በነኝህ ዋሶች አማካኝነት ከቁጥጥር እንዳይወጡ ለማረግ የተጠነሰሰ ተንኮል ነው ብለዋል::

በአገዛዙ የተሳሳተ ፖሊሲ ምክንያት ሥራ አጥ የሆኑትን ከ50 በመቶ በላይ የሆነውን የአገሪቱን ወጣቶች ድህረ ምርጫ 97 አደገኛ ቦዘኔ በማለት በጅምላ የጨፈጨፈ ፤ ያሰረና ያሳደደ አገዛዝ በግዴታ የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች አባል ከማድረግ ጀምሮ በትናንሽ ጊዜያዊ ጥቅም የገዛ ወገኖቻቸውን እንዲሰልሉ በህብረተሰቡ ውስጥ ለማሰማራት ተሞክሮ እንደነበር ነገር ግን እንዳልተሳካ ለማወቅ ተችሎአል።

ሪፖርተራችን ያነጋገራቸው አንዳንድ ወጣቶች የዛሬ 20 አመት ባዶ እግራቸውን ከጫካ የመጡ ወያኔዎች በዘረፉት ገንዘብ ሚሊዮነሮች ሲሆኑ እኛ በቀን አንዴ እንኳ መብላት የቅንጦት ያህል እየሆነብን መጥቶአል እና ይህቺ ያከፋፈሉን ገንዘብ እግራችን ላይ ያለቀቺውን ጫማና ዘግነቷን የቀየረቺውን የቀን ልብስ መቀየሪያ ስለምትሆነን የልባችንን በልባችን ይዘን ተቀብለናል። ምኞታችን የአገራችንን ሃብት የሚመዘብሩና ለድህነት የዳረጉን ሃይሎች ለፖለቲካ አላማ ሲሉ የሚወረውሩልን ድርጎ ተጠባብቆ መኖር ሳይሆን እኛም እንደዜጋ መብታችን ተጠብቆ ሰርተን የመኖር እና ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍል ስርዓት በአገራችን ሰፍኖ ማየት ነው ለርሱ ደግሞ የሚያስተባብረንና አመራር የሚሰጠን ካገኘን ለመነሳት ዝግጁ ነን ብለዋል።

### የወያኔ የመሬት ፖሊሲ ላይ ያለውን ጥያቄ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ቢወስንም አቃቤ ህግ ተብዬው በ ዕለቱ ሊቀርብ ባለመቻሉ ጉዳይ በሌላ ቀን እስኪታይ ተማሪ አስቻለው ወደ ዕስር ቤት እንዲመለስ መደረጉ በህግ ሽፋን ዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው ሰቆቃ ገደብ የለሽ መሆኑን ያሳያል ብለዋል።

ወያኔ በመላው አገሪቱ ያሰፈነውን አፈና ለማጠናከር ባለው ዕቅድ መሰረት ከመደበኛ ትምህር ቤቶች በህግ ትምህርት የተመረቁትን የህግ ባለሙያዎች ኮተቤ በሚገኘው ሲቪል ኮለጅ ተብሎ በተሰየመው የካድሬዎች ማሰልጠኛ ተመራቂዎች የተካ ሲሆን የነዚህ ታማኝ ካድሬ ዳኞች ዋና አላማ ወያኔ ያወጣቸውን ህጎችና ፖሊሲዎች ሊቃወሙ ይችላሉ ተብለው የሚጠረጠሩትን በፍርድ ቤት ሽፋን ወደ እስር ቤት መላክ እና ዜጎች በፍርሃትና በስጋት ተሸመድምደው ለስርዓቱ በታማኝነት እንዲገዙ ማስቻል መሆኑ በተደጋጋሚ ታይቶአል።

### ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ውጥረት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በመቀጠልም ወያኔ ገና ስልጣን እንደተቆጣጠረ በ1983 እና 1984 ዓም በግብጽ ዉሃ ልማት ምንስቴር የሚመራ የውሃ ኤክስፐርቶች ቡድን ኢትዮጵያ እየተመላለሰ በቀደሙት መንግሥታት ለማንም የግብጽ ባለሥልጣን ተከልክሎ የኖረውን የአባይን ምንጭ ከመሠረቱ ከጣና ጀምሮ እስከ ገባሮቹ ድርስ በሄሊኮፕተር ተዘዋወሮ እንዲጎበኝ ሲያደርግ እንደነበረና ከንጉሰ ነገስቱ ጊዜ ጀምሮ በአባይ ሸለቆ ላይ የተደረጉ ጥናቶች በሙሉ ከቀድሞው የውሃ ልማት ኮሚሽን መዝገብ ቤት በወቅቱ ጠ|ሚንስቴር በነበረው ታምራት ላይኔ ትዕዛዝ ተጭኖ እንደተወሰደ እና ለግብጽ አሳልፎ እንደተሰጠ አስታውሰው ፣ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ድህረ ምርጫ 97 በነበሩት 15 አመታት የኢትዮጵያን በአባይ የመጠቀም መብት ጠብ ያለሽ በዳቦ ነው እያለ ሲያናንቅ እና ጥረቱ የነፍጤኞችና ጦርነት ናፋቂዎች ሴራ ነው በማለት ሲያጥላላ እንደነበር የሚታወቅ ነው ብለዋል።

በራሷ ወንዞች መጠቀም ተስኖአት በየአመቱ በረሃብ ዜጎቿ የሚቀጠፉባት አገራችንን ከ20 አመት በላይ በመግዛት ላይ የሚገኘው ይህ ዘረኛ የትግራይ ጉጂሌ ቡድን የአባይ ሥም በተነሳ ቁጥር ሽንጡን ገትሮ ለግብጽ ሲከራከር እንዳልነበረ ዛሬ የሥልጣን እድሜው ማጠሪያ ቀን ሲቃረብ ለልማት ሃሳቢና አባይን ወንዝ ገዳቢ መስሎ ለመታየት መሞከሩ የኢትዮጵያን ባንዲራ ጨርቅ ነው ብሎ ሲያጥላላ ከኖረ ቦኋላ የህዝብ ጥላቻ ስሜት የቀየር መስሎት በአገሪቱ ታሪክ ያልነበረን የባንዲራ ቀን አክብሩ በማለት ላይ ታች ከሚለው ጋር ይመሳሰላል ብለዋል በማከል። ያላላ መስሎት አሁን የባንድራ ቀን ኢትዮጵያ መጠቀም የለባትም በማለት ለግብጾች ጥብቅና ቆሞ ነበር ብለዋል:: እኒሁ ባለሙያ አክለውም ወያኔ ዕድሜውን በሙሉ የአንድነታችንና የልማታችን መሠረት የሆኑትን ሁሉ ሲያንቋሽሽ እና ሲያፈርስ ከቆየ በሁአላ በተለይም ከ1997 ምርጫ ማግስት የደረሰበትን ኪሳራ ለማካካስና የህዝብንም ቀልብ በመሳብ ልማታዊ መስሎ ለመታየት አቅሙ የሚፈቅደውንና የማይፈቅደውን ነገር ሁሉ እሰራለሁ በማለት ህዝብ ባዶ የተስፋ ዳቦ እንዲገምጥ ይፈልጋል ብለዋል። አያይዘውም ወያኔ እውነተኛ የልማት ሃሳብ ቢኖረው ኖሮ የአርባ ምንጭ ውሃ ቴክኒዮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና አላማው የኢትዮጵያን ወንዞች ባግባቡ የመጠቀም ስራ መሆኑ እየታወቀ ኢንስቲትዩቱ እንዲፈርስ ማድረግ አልነበረበትም ብለዋል::

የወያኔ ዋናው አላማ የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ሲል ህዝብ እንደሰሜን አፍሪካው ሆ ብሎ እንዳይነሳበት የሃሰት ፕሮፖጋንዳ መመገብ ለዚሁም ስለ አምስት አመት የትራንስፎሜሽን ዕቅድ ከመደስኮር ጎን አገሪቱ በባቡር መንገድ ፤ በ ኤሌክትሪክ፤ ከመምነሽነሽ ጀምሮ የኒውክላር ሃይል ባለቤትም እናደርጋታለን የሚል ባዶ ፕሮፖጋንዳ በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ማሰራጨት ተጀምሮአል።

### ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ አመጽ በድንገት መነሳቱ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እንደ ኢሳት ዘገባ በስብሰባው የተሳተፉ ነጋዴዎች አርብ እለት የከተማው ባለስልጣናት ከ200 የማያንሱ ነጋዴዎችን ሰብስበው በከተማው ሊሰበስቡ ስላሰቡት የግብር መጠን ገለጻ አድርገዋል። ባለስልጣኖቹ በወረዳው ከዚህ ቀደም በአመት 4 ሚሊዮን ብር እንደሚሰበሰብ አስታውቀው ፣ በዚህ አመት አመት ግን መጠኑን በ5 እጥፍ በመጨመር 20 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ማቀዳቸውን ገልጸዋል።

ይህን የሰሙ ነጋዴዎች በአንድ ድምጽ የተቃውሞ ድምጽ በማሰማት እቅዱን ውድቅ ያደረጉ ሲሆን ፣ አንድ ነጋዴም እስከዛሬ ከአቅማችን በላይ የሆነ ክፍያ ስንከፍል ቆይተናል፤ አሁን ደግሞ ይህን ይህን ያክል ገንዘብ ክፈሉ ትሉናላችሁ ፤ ጭራሽ የምንበላው ልታሳጡን እና በርሀብ ልትጨርሱን ነው ወይ ሲሉ ተቃውሞአቸውን ገልጸዋል።

የህዝቡ ተቃውሞ ያስደነገጣቸው የመንግስቱ ባለስልጣናትም መንግስት በአምስት አመቱ የትራንስፎርሜሽን እቅድ ባቡር እንደሚገነባ፣ የኒውክሊየር ሀይል ለመገንባትም ማቀዱን በመግለጽ ህዝቡ እንደምንም ብሎ የተጣለበትን እዳ እንዲከፈል ጠይቀዋል። በመጨረሻም ነጋዴዎች መንግሰት ልማት እያለማሁ ነው ይላል እንጅ ድህነት ሲስፋፋ ከማየት በስተቀር ምንም አይነት ልማት እስካሁን ድረስ ሲለማ አላየንም በማለት የመንግስትን እቅድ መቃወማቸውን ገልጸዋል።

በሌላ በኩልክ ደግሞ እጂግ በርካታ ኢትዮጵያዊያን በችግር በሚሰቃዩበት በአሁኑ ሰአት የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት አዘጋጂተውት በነበረ ጭፈራ ላይ የአገዛዙ ጥጋበኞች ርስ በርስ በጥይት የተደባደቡ መሆኑን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ዘግቡአል::

በኢትዮጵያ ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ቦታዎች ከፍተኛ የሆነ አለመረጋጋትና ግጭቶች እየተከሰቱ መሆኑ በተደጋጋሚ የተዘገበ ሲሆን ጉዳዩን አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡን የጠየቅናቸው አንድ የፖለቲካ ተንታኝ በሰጡን አስተያየት ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን እየታየ ያለው ሁኔታ የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ የስልጣን ዘመን ያለቀበት ምእራፍ አመላካች ነው ካሉ በሁዋላ፣ የአገዛዙ ባለስልጣናት ህዝቡን በእስራት፣ በድብደባና በተለያዩ ማስፈራሪያ መንገዶች አፍኖ ለመግዛጥ ጥረት ቢያደርግም አንድ ቀን ሁሉም ነገር ከቁጥጥሩ ውጭ እንደሚሆንና ህዝባዊ አመጹ ተቀጣጥሉ አገዛዙ ከኢትዮጵያዊያን ትከሻ ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተሽቀኝጥሮ እንደሚጣል ጥርጥር የለኝም ብለዋል::

### የዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ አገዛዝ መልእክተኞች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከዚህ በተጨማሪ በበርካታ የመረጃ ድረ ገጾች የሚወጡ ጽሁፎች እንደሚያመለክቱት በቅድሚያ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን ተበሎ የተጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ከቅርብ ቀናት ወዲህ በየሃገራቱ የሚገኙት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ስብሰባውን ለተወሰኑ የስርአቱ ግብረ አበሮች ብቻ እንዲወስኑ እያስገደዳቸው እንደሆነ ያሳያል። በውይይቱ እንዳይሳተፉ የተገለሉት ኢትዮጲያዊያንም በቀኑ ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ እንደሚያደርጉና ለኢህአዴግ መራሹ አገዛዝ ለሆዳቸው ያደሩትን ግለሰቦች ምስል በመቅረጽ ለአለምና ለኢትዮጲያ ህዝብ እንደሚያጋልጡ የሰልፉ አዘጋጆች ይፋ አደርገዋል።

በሰሜን አሜሪካ የሚካሄደውን ስብሰባ ለመቃወም በርካታ የተቃዋሚ ድርጂቶችና ግለሰቦች በስፋት እየተንቀሳቀሱ ሲሆን ዓለም አቀፍ የሲቪክ ንቅናቄ ለለውጥ በኢትዮጵያ፣ ማርች ፎር ፍሪደም፣ የጋራ እንቅስቃሴ ለአዲሲቱአ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የዘረኛው አገዛዝ ተቃዋሚዎች በሰልፉ እንደሚሳተፉ ባወጡአቸው መግለጫዎች አስታውቀዋል::

ማርች ፎር ፍሪደም - እምቢ ለነጻነቴ! እምቢ ለሰባዊ ክብሬ! እምቢ ለአንድነቴ ብለን በጋራ እንነሳ!!! በሚል ርእስ ባወጣው መግለጫው በሃገርና በንጹሃን ወገኖቻችን ደም እየነገደ፣ ቀኑ እየመሸበት ያለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የባለስልጣናቱ የሰሜን አሜሪካ ተልእኮ ዋና አላማ ለልማት ወይስ እኛን በሆድ ከፋፍለው የነርሱ የጥቅም ምርኮኞች ሆነን፣ የህልም እንጀራ እየበላን፣ ለለውጥ እንዳንጮህ ጸጥ ረጭ አርገው ለዘላለም ለመግዛት፣ በማለት ከጠየቀ ቦኋላ ልብ ያለው ልብ ይበል!!! በማለት አሳስቦአል።

በማስከተልም የኢትዮጵያ ህዝብ በኢሃዴግ የመለስ ዜናዊ ብልሹ አስተዳደርና አምባገነናዊ አገዛዝ ስር ወድቆ በኑሮ ውድነትና በርሃብ አለንጋ እየተገረፈ፣ ሰባዊና ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተረግጦ ለአፈናና ለእስራት እየተዳረገ ሉአላዊ ክብሩ ተደፍሮ ለም መሬቱና አንጡራ ሃብቱ ለባእድ እየተሸጠ በገዛ ሃገሩ ተፈናቃይና የውጪ እጅ ተመልካች ሆኖ ለስደትና ለእንግልት እየተዳረገ እነሆ ዛሬ ሃያ የሰቆቃ የእልቂትና የመከራ ዓመታት አስቆጥሩአል:: አሁንም በደሉ በባሰና በተቀነባበረ መልኩ እየቀጠለ እንጂ እየበረደ አይደለም:: ህዝባችን ከድህነት መስመር በታች ወርዶ የዓለም የስልጣኔ ጭራ ሆኖ ይገኛል ብሉአል::


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org